4ኛ ዓመት ቁጥር 13
4[Th] Year-No. 13

ሐረር ነሐሴ 24/1991
Harar August 30/1999

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

*HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE*

| | | |
|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ ብር 1:00 | በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272 |



**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር 18/1991

የሀረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሀረሪ ቋንቋ ፊደላትንና የቋንቋውን አጻጻፍ ሥርዓት ወጥ ለማድረግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 18/1991 ________ ገጽ 166


## አዋጅ ቁጥር 18/1991 ዓ.ም

## የሀረሪ ቋንቋ ፊደላትንና የቋንቋውን አጻጻፍ ሥርዓት ወጥ ለማድረግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 18/1991

የሀረሪ ቋንቋ ፊደላትንና የቋንቋውን አጻጻፍ ሥርዓት ወጥ በሆነ ሁሉም በጋራ ሊከተለው በሚገባ አግባብ ለመወሰን በማስፈለጉ፣

የክልሉ ብሔራዊ ቋንቋና ከክልሉ መንግሥት የሥራ ቋንቋ አንዱ የሆነውን የሀረሪ ቋንቋ ደረጃውን ጠብቆ ለማሳደግና ለማጎልበት እንዲቻል፣

ለዚህ ሥራ ዝግጅት ሲባል የሀረሪን ቋንቋ በጽሁፍ ላይ ለማስፈር የግእዝ ፊደል ቀደም ሲል ተመርጧል፣

እንደተባለው የግእዝ ፊደላት የሀረሪን ቋንቋ ለመጻፍ በጣም አመቺ ሆነው ቢመረጡም በውስጡ ያሉ ፊደላትን ሙሉ በሙሉ እንዲጸሉ አልተወሰዱም በሀረሪ ቋንቋ ውስጥ ድምጽ የሌላቸው ተትተዋል። ተደጋጋሚ ከሆኑት እንደነ ሰ፣ ሠ፣ አ፣ ዐ፣ ሐ፣ ሀ፣ ኀ፣ ለሀረሪ ቋንቋ ያመቻሉ የተባሉ ብቻ ተመርጠው ተቀምጠዋል፣

በተጨማሪም ለሐረሪ ቃላት አጻጻፍ ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ለማስወገድ ተሞክሯል። ድምጽ ሲረዝምና ሲያጥር ሲጠብቅና ሲላላ ሲከፈትና ሲዘጋ ሊፈጠር የሚችሉ የአጻጻፍ ልዩነቶችንም እሳቤ ውስጥ በማስገባት በህግ መልክ ለማስቀመጥ ተሞክሯል፣

በሀረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ህገ-መንግሥት አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሀረሪ ብሔራዊ ጉባኤ የሚከተለውን አዋጅ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

## አንቀጽ 1

## አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የሀረሪ ቋንቋ ፊደላትንና የቋንቋውን አጻጻፍ ሥርዓት ወጥ ለማድረግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 18/1991 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## አንቀጽ 2

## ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "የሀረሪ ፊደላት ማለት" የሀረሪ ፊደላት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 የተመለከቱት 24 ፊደላት ናቸው።
2. "የሥራ ቋንቋ ማለት" በክልሉ ህገ - መንግሥት አንቀጽ 5 መሠረት የተወሰነው የሀረሪና የኦሮምኛ ቋንቋ ነው።
3. "የሀረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ማለት" በክልሉ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 29 የተመለከተው የሀረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ነው።

## ክፍል ሁለት

## አንቀጽ 3

## የሀረሪ ፊደላት

የሀረሪ ፊደላት ሃያ አራት /24/ ናቸው ።

እነሱም፡-

ሐ ለ መ ረ ሰ ሸ

ቀ በ ተ ቸ ነ ኘ

አ ከ ኸ ወ ዘ የ

ደ ጀ ገ ጠ ጨ ፈ

ናቸው።

## አንቀጽ 4

## የተውሶ ፊደላት

የሀረሪ ቋንቋ ከዚህ የሚከተሉትን ፊደላት በተውሶ ይጠቀማል። እነሱም የሚከተሉት ዘጠኝ /9/ ፊደላት ናቸው ።

ሀ ዐ ፀ ጸ ሠ ጰ ሽ

ዠ ፐ ናቸው።

## አንቀጽ 5

## የአጻጻፍ ሥልት /ሥርዓት/

የሀረሪ ቋንቋ የአጻጻፍ ሥልት ከዚህ አዋጅ ጋር አባሪ በሆነው ዝርዝር መሠረት ይሆናል።

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## አንቀጽ 6

## የሀረሪ ቋንቋ አካዳሚ ኃላፊነት

የሀረሪ ቋንቋ አካዳሚ ይህን አዋጅ የማስፈጸም ኃላፊነት አለበት።

## አንቀጽ 7

## አዋጁን የመከተል ግዴታ

የሀረሪን ቋንቋ የሚጠቀሙ ማናቸውም የክልሉ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ግለሰቦች ይህንን አዋጅ የመከተል ግዴታ አለባቸው።

## አንቀጽ 8

## አዋጁ ስለሚሻሻልበት ሁኔታ

ይህ አዋጅ የሚሻሻለው የማሻሻያው ሃሳብ በአካዳሚው ተዘጋጅቶ በሀረሪ ብሔራዊ ጉባኤው ሲጸድቅ ብቻ ነው።

## አንቀጽ 9

## ደንብ የማውጣት ሥልጣን

ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም አስፈላጊው ደንብ በአካዳሚው ረቂቁ ከተዘጋጀ በኋላ በሀረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ጸድቆ ይወጣል።

## አንቀጽ 10

### ተፈጻሚነት የሌላቸው ህጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚጻረር ማንኛውም ህግ ይህን አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ተፈጻሚነት የለውም።

## አንቀጽ 11

### አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በሀረሪ ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ጥር 1992
ሀረር
ጋዛሊ መሐመድ አዱስ
የሀረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ
መንግሥት
ፕሬዝዳንት

# ሀረሪ መሐድ መጅሊስ

## 1. ሀረሪ ሐርፊ

ሐ ለ መ ረ ሰ ሸ ቀ በ

ተ ቸ ነ ኘ አ ከ ኸ ወ

ዘ የ ደ ጀ ገ ጠ ጨ ፈ

## 2. ሊቋሕ ሐርፋች

ሀ ـه________

ዐ ع________

ፀ غ________

ጸ ص________

ሠ ث________

ጰ ________

ቨ ________

ዠ ________

ፐ ________

## 3. ዚመከተብ ሑይረ

### 3.1 ሐጪይር ጠባች

አ__________ በለለ፣ ሰበረ፣ ከተበ፣ መሐጠ፣ ወኸበ

ኡ__________ በለኡ፣ ሱቡር፣ ፉር፣ ቡን፣ መሉ

ኢ__________ ኢቢእ፣ ፊዝ፣ ዚቅ፣ ሀረሪ፣ ኪልኪላት

ኤ__________ ኢሔ፣ ኤሔር፣ ከርሴ፣ ፈተሔ፣ ጋሬ

እ__________ እኹሌ፣ ሰደቦ ፣ በለእ፣ ኮእት

### 3.2 ጉዶውር ጠባች

አ __________ አለ፣ አባት፣ ባር፣ ኪታብ ፣ ሰበራ?

ኡው________ ኡውን፣ ቡውር፣ ፉውር፣ ቡፉውሪ፣ ሑውል፣ አቡውረ

አው__________ አውር፣ ሶውር፣ አቦውች፣ ሰበሮው? ኢንዶውች

ኢይ__________ ኢይን፣ ፊይዝ፣ ቢሊይት፣ ፊይት፣ ሐሪይር

ኤይ________ ኤይመደ፣ ኤይለድ፣ ዌይር፣ ፈተሔይ?

### 3.3 ጠቢይቅ ጠበ

አልለ፣ ጢልለ፣ አሰሱ ፣ አረራት፣ አርረ

አርራ ፣ ቢርሪኝ፣ ቦውከኪ፣ ወሕሓጠ

ፈርራትቱ፣ ሐጅጃጂን፣ ኪዝበኝኘ

### 3.4 ሊከሪይም /ጠበ መርገዝሌ/

ጸላት፣ ሴይላት፣ አው፣ ከርከድደን፣ ሰርሰር

አፍዲይጀ፣ መርመር፣ ሙርሙር፣ ፉሉሕ፣ አሕ፣ ዊሕጢ

## 4. ቀጠብቲ፡-

ፉይ ቤይቀድሌ ዲፐሎውመቤ ዚትከተበ ሱም ኻነ ጊር ኩቱብዞውው እልመናወፐ። እልታ ጊር ሞው ፉይ ሐጂይስ መከተብ ሔይረቤ መከተብ የትኺይሻል። ሚሳሊሌ፡-

ዐሊ ፤ አሕመድ ፤ ዩውሱፍ፤ ዐብዱልፀፉውር፤ ሀረሪ፤ አውሓኪም

## 5. ሀረሪ ሐርፊ መሕዲይጀ ሉውሕ

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |